# የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን መመሪያ
# ቁጥር 902/2014

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን

ግንቦት 2014 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

*የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር አብሮ በመጓዝ ከምድር ወደ አየር፣ ከኬብል እና ከሳተላይት የማሰራጫ መንገዶች በተጨማሪ በበይነ-መረብ አማካኝነት በስፋት በመሰራጨት አማራጭ የመረጃ ምንጭ፣ የአመለካከትና የሃሳብ ብዝሃነት ማስተናገጃ፣ የልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ማከናወኛ እንዲሁም የገቢ ማስገኛ ዘዴ መሆኑን በመገንዘብ፤ ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር የሚጣጣም መመሪያ በማውጣት የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃንን ዕድገት ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤*

*ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን፣ ሃሳቦችንና አመለካከቶችን በነፃ ማንሸራሸራቸውን ከማረጋገጥ፣ ጥበቃ ከማድረግ እንዲሁም የዘርፉን እድገት ከማረጋገጥ አንፃር በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር* 1238/2013 *የተዘረጋውን የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን የምዝገባ፣ የክትትልና ድጋፍ አሰራሮች በዝርዝር መመሪያ ማስፈፀም በማስፈለጉ፤*

*በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር* 1238/2013 *አንቀፅ* 6(3) *እና አንቀፅ* 27 *መሠረት በበይነ-መረብ አማካኝነት የሚሰራጩ የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች ወይም የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ይዘት አሰራጮች ማንነታቸውን በይፋ እንዲገልጹ ወይም በባለሥልጣኑ እንዲመዘገቡ በመደንገጉ፤ የምዝገባ ሥርዓት ሒደቱን ግልፅ፣ ፍትሐዊ፣ የሃሳብና የመረጃ ብዝሃነትን የሚያስፋፋ ማድረግ እንዲሁም በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ አንቀፅ* 6(5) *መሠረት የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪዎች የአገሪቱን ሕጎች ባከበረ መልኩ ሥራቸውን ማከናወናቸውን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤*

*በተመሳሳይም የባለሥልጣኑን የሥልጣን ክልል በግልፅ በመመሪያ መወሰን በማስፈለጉ፤*

*በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር* 1238/2013 *አንቀፅ* 12(7) *እንዲሁም አንቀፅ* 90(2) *መሠረት ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ቦርድ ወጥቷል፡፡*

## *ክፍል አንድ*
## *ጠቅላላ*

1. ***አጭር ርዕስ***

   *ይህ መመሪያ "የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን መመሪያ ቁጥር 902/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡*

2. ***ትርጓሜ***

   *የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-*

   1/ *"የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን" ማለት በኢንተርኔት አማካይነት የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎትን ለሕዝብ ለማቅረብ በተቋቋመ እንዲሁም በይዘት ላይ*

የመወሰን ኃላፊነት ባለው የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት አቅራቢ የሚከናወን፣ ዋነኛ ሥራውም ዜና፣ ፕሮግራም ወይም የድረ-ገፅ ፅሁፍ ማሰባሰብ፣ ማዘጋጀትና ማሠራጨት የሆነ፣ እንዲሁም ምስል፣ ድምፅ፣ ቪድዮ እና የድረ-ገፅ ፅሁፍን ወይም እነዚህን በማቀናጀት በኢንተርኔት አማካይነት የሚሠራጭ የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሲሆን፣ የሚከተሉትን አያካትትም፡-

ሀ) በበይነ-መረብ የሚሰራጭ መፅሀፍን፣

ለ) የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ ሙሉ በሙሉ የሚሰራጭበት እስካልሆነ ድረስ ማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃንን፣

ሐ) የበይነ-መረብ ግለሰብ ጦማሮችን፣

መ) የበይነ-መረብ ጋዜጣና መፅሔት አካል ያልሆነ ፎቶ፣ ሥዕልና ካርቱንን፣

ሠ) በግለሰቦች መካከል የሚደረግ የበይነ-መረብ መረጃ ልውውጥን፣ እና፣

ረ) የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ለመስጠት ባልተቋቋሙ ተቋማት የሚሰራጭ የድረ-ገፅ ይዘት፡፡

2/ ***"የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት"*** ማለት በየጊዜው የሚወጣ ኅትመትን፣ የብሮድካስት አገልግሎትን እና የበይነ-መረብ የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የዜና ወይም የፕሮግራም ወይም የዜና እና የፕሮግራም አገልግሎት ለሕዝብ ለማቅረብ የተቋቋሙ አካላትን ያካትታል፡፡

3/ ***"ዋና አዘጋጅ"*** ማለት የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ያለበት የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

4/ ***"ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት"*** ማለት በዜና ወይም በፕሮግራም መረጣ ወይም አቀራረብ ላይ ውጤታማ ቁጥጥር ማድረግ ወይም ይዘትን መወሰን ማለት ነው፡፡

5/ **"አመልካች"** ማለት በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ሥራ ለመሰማራት የሚያስችል የምዝገባ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ያመለከተ ሰው ነው፡፡

6/ ***"የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ"*** ማለት በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት የበይነ-መረብ አገልግሎት ለመስጠት በባለሥልጣኑ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

7/ ***"ዜና"*** ማለት አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ አገራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው እና ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮችን በሚመለከት በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አማካይነት የሚቀርብ የዘገባ ሥርጭት ነው፡፡

8/ ***"ፕሮግራም"*** ማለት በየ24 ሰዓቱ ወይም ሰፋ ያለ ጊዜ ጠብቆ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በድምፅ፣ በምስል ወይም በድምፅና በምስል ተቀነባብሮ በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አማካይነት የሚቀርብ ዝግጅት ነው፡፡

9/ ***"የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል"*** ማለት የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብን ማመልከቻ

ተቀብሎ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች መሟላታቸውን በማጣራት የሚመዘግብና የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚሰጥ በባለሥልጣኑ ውስጥ የተቋቋመ መደበኛ የሥራ ክፍል ነው፡፡

10/ ***"ባለሥልጣን"*** ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ነው፡፡

11/ ***"ቦርድ"*** ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ቦርድ ነው፡፡

12/ ***"የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ"*** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

13/ ***"አዋጅ"*** ማለት የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 ነው፡፡

14/ ***"ሰው"*** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

15/ ሌሎች በአዋጁ የተሰጡ ትርጉሞች ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡፡

16/ በወንድ ፆታ የተገለፀው አገላለፅ የሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. *<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>*

ይህ መመሪያ በኢትዮጲያ ውስጥ በተቋቋመ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## *4. <u>የመመሪያው መርሆች</u>*

1/ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ሰው በግል ወይም የሕግ ሰውነት ባለው አካል ግልፅ በሆነ መስፈርትና ያለአድልኦ በመመዝገብ እንዲሁም የምዝገባ ምስክር ወረቀትና ሕጋዊ እውቅና በማግኘት የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ለመስጠት ያለውን መብት ማረጋገጥ፤

2/ ከመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት የቴክኖሎጂ እድገት ጋር የሚጣጣም መመሪያ በማውጣትና የዘርፉን ሚና በማጎልበት የዜጎችን የመረጃ ተደራሽነት ማረጋገጥ፤

3/ በአዋጁ መሠረት የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ማንነታቸውን ለሕዝብ በይፋ የሚያሳውቁበትን የምዝገባ ሥነ-ሥርዓት መዘርጋት፤

4/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን የአገሪቱን ሕጎች ባከበረ መልኩ ሥራቸውን ማከናወናቸውን ማረጋገጥ፤

5/ የባለሥልጣኑን የሥልጣን ክልል በግልፅ በተገደበ ሁኔታ መካሄዱን ማረጋገጥ፡፡

## *5. <u>ስለበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት</u>*

1/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ሰው በግሉ ወይም በድርጅቱ፣ አማካኝነት የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ባለቤት የመሆን መብት አለው፡፡

2/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው ማንኛውም አካል የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ባለቤት የመሆን መብት አለው፡፡

3/ 25 በመቶ የሆነ የአክስዮን ድርሻው በውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት የተያዘና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ድርጅት የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ባለቤት የመሆን መብት አለው፡፡

4/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው አንድ የንግድ ድርጅት በድርጅቱ ባለቤትነት ሥር የሚተዳደሩ አንድ የቴሌቪዥን፣ አንድ የሬዲዮ፣ አንድ የጋዜጣ፣ አንድ የመፅሔት እና አንድ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ማቋቋም ይችላል፡፡

5/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥን፣ የጋዜጣ ወይም የመፅሔት ባለቤት የሆነ ድርጅት በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣ ወይም በመፅሔት ያሰራጨውን ዜና፣ ፕሮግራም ወይም የኅትመት ውጤት በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን የሚያሠራጭ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት የመመዝገብ ግዴታ አይኖርበትም፡፡

6/ ማንኛውም መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም አካል በሕግ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ወይም የተቋቋመበትን ዓላማ ለማራመድ ዜና፣ ፕሮግራም ወይም የኅትመት ውጤት በተቋሙ ድረ-ገፅ ወይም በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን የሚያሠራጭ ከሆነ ሕጋዊ እውቅና እንዳገኘ ተቆጥሮ በዚህ መመሪያ መሠረት የመመዝገብ ግዴታ አይኖርበትም፡፡

## ክፍል ሁለት
## የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ምዝገባ ሥነ-ሥርዓት

### 6. የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ምዝገባ አመልካች

1/ በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት እና በአዋጁና በመመሪያው የተዘረዘሩትን መረጃዎች በማሟላት የምዝገባ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ማመልከት ይችላል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ምዝገባ ማመልከቻና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት በቴክኖሎጂ ታግዞ እንዲከናወን ማድረግ ይኖርበታል፡፡

### 7. ስለምዝገባ ማመልከቻ ቅፅ

ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች የያዘ የምዝገባ ማመልከቻ ቅፅ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ የማመልከቻ ቅፁንም በድረ-ገፁ ተደራሽ በማድረግ ተሞልቶ እንዲቀርብ አማራጭ መንገድ ይፈጥራል፡፡

1/ የመስራቹ፣ የባለቤቱ ወይም የአመልካቹ ድርጅት ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ ድርጅቱ የተቋቋመበት ሀገር፤ ስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻ፤

2/ የባለቤትነት ሁኔታ፤

3/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤

4/ የንግድ ፈቃድና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤

5/ የዋና አዘጋጅ ስምና አድራሻ፤

6/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ የአክስዮን ባለቤቶች ስም ዜግነት፣ አድራሻና ድርጅቱ የተቋቋመበት ሀገር፣ መመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፤

7/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ መጠሪያ ስም፣ አገልግሎቱ የሚሠጥበት ቦታና አድራሻ፤

8/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ ዶሜይን ስም፤

9/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ የዶሜይን ስም ባለቤትነት ማረጋገጫ፤

10/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ የቢሮ ስልክ ቁጥር፤ የኢሜል አድራሻ፤

11/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ የሚጠቀምበትን የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ስም፤ የኢሜል አድራሻ እና የማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን አድራሻ፤

12/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ የሚጠቀምበት የኢንተርኔት ሰርቨር አገልግሎት አቅራቢ ወይም የማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን ወይም የቻናል ባለቤት ወይም አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ስም፤ የኢሜል አድራሻ እና የማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን አድራሻ፤

13/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ድርጅቱ ሌላ ጋዜጣ፣ መፅሄት፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ያለው ስለመሆኑ፤

14/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎቱ ዓላማ፣ የፕሮግራሙ አይነት፣ የሚሰራጭበት ቋንቋ፣ የሥርጭት ቀን፣ ሰአትና አጠቃላይ ሁኔታ፣

15/ ሌሎች አገልግሎቱን እና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎች፡፡

## 8. ከማመልከቻ ቅፅ ጋር ተያይዘው ስለሚቀርቡ ሰነዶች

አመልካቹ የሚከተሉትን ሰነዶች በማሟላት ከማመልከቻ ቅፁ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

1/ የመስራቹ፣ የባለቤቱ ወይም የአመልካቹ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ኮፒ፤

2/ የዋና አዘጋጁን መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ኮፒ፤

3/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤ የንግድ ፈቃድና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤

4/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነም በሠነዶች አረጋጋጭ አካል የተረጋገጠ የመመሥረቻ ፅሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብ፤ የአክስዮን ባለቤቶች መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒ፣

5/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ ከኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪው ወይም የኢንተርኔት ሰርቨር አገልግሎት አቅራቢው ወይም ከማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን ወይም ከቻናል ባለቤቱ ወይም ከመሰል የኢንተርኔት አገልግሎት

አቅራቢ ድርጅት ጋር ያደረገው ውል ወይም ስምምነት ካለው የስምምነቱን ኮፒ፡፡

## 9. *የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መረጃዎች*

የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1/ አመልካቹ ግለሰብ ከሆነ የመስራቹ፣ የባለቤቱ እና የአመልካቹ ድርጅት መጠሪያ ስም፣ ዜግነት፣ የተቋቋመበት ሀገር፣ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒና 2 ጉርድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ፤

2/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት የተረጋገጠ የመመሥረቻ ፅሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብ፤ የአክስዮን ባለቤቶች ስም፣ የዜግነት ሁኔታ፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻ፤ ድርጅቱ የተቋቋመበት ሀገር፣ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ኮፒና 2 ጉርድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ፤

3/ ማመልከቻው የቀረበው በወኪል ከሆነ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት የተረጋገጠ የውክልና ሰነድና መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ኮፒና 2 ጉርድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ፤

4/ ዋና አዘጋጅ ካለው የዋና አዘጋጁን ስምና አድራሻ፤ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ኮፒና 2 ጉርድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ፤

5/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ መጠሪያ ስምና አገልግሎቱ የሚሠጥበት ቦታና አድራሻ፤

6/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የንግድ ፈቃድና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤

7/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ ዶሜይን ስም፤

8/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ የዶሜይን ስም ባለቤትነት ማረጋገጫ፤

9/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ የቢሮ ስልክ ቁጥር፤ የኢሜል አድራሻ፤

10/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ የሚጠቀምበት የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ስም፤ የኢሜል አድራሻ፤

11/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ የሚጠቀምበት የኢንተርኔት አገልግሎት ሠጪ የማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን ስምና አድራሻ ወይም የቻናል ባለቤት ወይም መሰል የኢንተርኔት አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት ስም፤ የኢሜል አድራሻ፤

12/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ ድርጅት ከኢንተርኔት አገልግሎት አቅራቢው ወይም ከማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃኑ ወይም ቻናል አቅራቢው ጋር የተደረገ ስምምነት ካለው የስምምነቱን ኮፒ፤

## 10. *የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ምዝገባ ሥነ-ሥርዓት ሒደት*

የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ምዝገባ ሒደት የሚከተለውን የሥራ ፍሰት ጠብቆ ይከናወናል፡-

1/ በበየነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በማናቸውም ጊዜ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የምዝገባ ማመልከቻ ቅፅ በመሙላት እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 እና 9 የተዘረዘሩትን መረጃዎች በማሟላት የምዝገባ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ያቀርባል፤

2/ የባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል የምዝገባ ማመልከቻ እንደቀረበለት፡-

ሀ) አመልካቹ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መረጃዎችን ማሟላቱ ከተረጋገጠ ምዝገባ በማከናወን የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ይሰጣል፤

ለ) በአዋጁና በመመሪያው ከተዘረዘሩት መረጃዎች ውስጥ ያልቀረቡለት መረጃዎች ካሉ ተሟልተው እንዲቀርቡ ለአመልካቹ በፅሁፍ ያሳውቃል፤ ተሟልቶ በቀረበለት ጊዜ በመመዝገብ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

ሐ) አመልካቹ በአዋጁና በመመሪያው የተዘረዘሩትን መረጃዎች ለማሟላት አለመቻሉን በማረጋገጥ የምዝገባ ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ወይም የምዝገባ ምስክር ወረቀት እንዳይሰጥ ሲወስን ውሳኔውን ከነምክንያቱ ወዲያውኑ ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

መ) አመልካቾች በፍትሐዊነት መስተናገዳቸውን ለማረጋገጥ ተመሳሳይና በቂ መረጃ ይሰጣል፤

3/ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እንዲወስድ የተገለፀለት አመልካች በአገልግሎት ክፍያ ደንብ የሚተመነውን የማመልከቻና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ክፍያ በመፈፀም የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይወስዳል፤

4/ አመልካቹ ማሟላት ያለበትን መስፈርት አሟልቶ ቀርቦ በ30 ቀናት ውስጥ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ካልተሰጠው ሕጋዊ እውቅና እንዳገኘ ይቆጠራል፤ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እስከሚሰጠው ሳይጠብቅም ወደ ሥራ መግባት ይችላል፤

5/ አመልካቹ ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለንግድ ሚኒስቴር ወይም ለክልል ንግድ ቢሮ በማቅረብ ማስመዝገብ አለበት፡፡

## 11. *ተቀባይነት ስላላገኘ የምዝገባ ማመልከቻ እና የዕድሳት ጥያቄ*

1/ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ ውድቅ ሊያደርግ የሚችለው አመልካቹ፡-

ሀ) በአዋጁና በዚህ መመሪያ ሊያሟላ የሚገባውን መረጃ ካለቀረበ፤ ወይም፣

ለ) ለበይነ-መረብ የመገናኛ ብዙሃኑ የሰጠው ስም አስቀድሞ የተያዘ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

2/ አመልካቹ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 10(2)(ሐ) እና 12(2) መሠረት ማመልከቻው በማናቸውም ምክንያት ውድቅ ከተደረገበት በማናቸውም ጊዜ ለባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በማመልከት ምላሽ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፤ የበላይ ኃላፊውም ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

3/ አመልካቹ የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው በበላይ ኃላፊው ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል።

4/ ቦርዱም የአመልካቹ አቤቱታ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና የውሳኔውን ቅጂም በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ መስጠት አለበት፡፡

5/ በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡

12. ***የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለማሳደስ***

1/ የበየነ መረብ መገናኛ ብዙሃን የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀት በየአመቱ ይታደሳል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ የእድሳት ማመልከቻ እንደቀረበለት፤ አመልካቹ በአዋጁና በመመሪያው መሰረት የዕውቅና ምስክር ወረቀት ለማግኘት ያቀረባቸው መረጃዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀቱን ወዲያውኑ ያድሳል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ መብትና እና ግዴታዎች

13. ***የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ መብቶች***

1/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ፦

ሀ) ተግባሩን በነፃነት የማከናወን፤ ነፃና የተለያዩ አመለካከቶች የሚንጸባረቁበትን ምህዳር የመፍጠር እና ለሃሳብ ልውውጥ መጎልበት አስተዋፅኦ የማድረግ መብት አለው፤

ለ) ኤዲቶሪያል ነፃነቱ የተጠበቀ ነው፤ በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም ሰው ነፃና ገለልተኛ ነው፤

ሐ) ከማናቸውም አካል ዜና ወይም መረጃን የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት፤ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ወይም ትችት የማቅረብና ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎችን፣ መሣሪያዎችን የመጠቀም መብት አለው፤

መ) የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሕዝብን አስተያየት በመቅረጽ ሒደት የመሳተፍ መብት አለው፤

ሠ) በመገናኛ ብዙሃን ተቋሙ ነፃነት ላይ የሚከሰት ጣልቃ ገብነት፣ ተፅዕኖ፣ ጥቃትንና የደኅንነት ስጋትን ጨምሮ ሕገ መንግሥቱን በመፃረር የፕሬስ ነፃነትን የሚያደናቅፍ አሰራር ከተፈፀመበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፤

ረ) በመረጠው ሕጋዊ መንገድ የመደራጀት መብት አለው፤

ሰ) በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ አንቀፅ 49 ከተመለከተው ውጪ ማንነቱ እንዳይገለጽ በመስማማት መረጃ የሰጠን ምንጭ እንዲገልፅ አይገደድም፤

ሸ) በዚህ መመርያ በግልፅ የተመለከቱ መስፈርቶችን በማሟላት ምዝገባ እና የምዝገባ ምስክር ወረቀት እድሳት የማግኘት መብት አለው፡፡

2/ ባለሥልጣኑ ለበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ መብቶች ተግባራዊነት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፡፡

## 14. *የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ ግዴታዎች*

በአዋጁ መሠረት ማንኛውም የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1/ ፀያፍና የብልግና ቋንቋ አለመጠቀም፤

2/ ያታን፣ ብሔርንና ሃይማኖትን መሠረት በማድረግ የጥላቻ ስሜት እንዲፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርግና ግጭት የሚያነሳሳ ዘገባን አለማሰራጨት፤

3/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ ራሱ አዘጋጅቶ ከሚያሰራጨው ይዘት የተለዩና ከሦስተኛ ወገን፣ ከተባባሪዎች፣ ልዩ ፍላጎት ካላቸው ቡድኖችና ከማስታወቂያ አስነጋሪዎች የሚመነጭ ይዘትን በግልፅ ለይቶ ማቅረብ፤

4/ የሚያሰራጨው ይዘት ሚዛናዊ፣ ፍትሐዊ እና ብዝሃነት ያላቸው ድምፆችን ያካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ጥረት ማድረግ፤

5/ የሚያሰራጨው ይዘት ለሕፃናትና ለነፍሰጡር ሴቶች ተገቢ መሆኑን ለማረጋገጥ ይዘቱ ለማን እንደማይሆን አስቀድሞ ማሰወቅና ተጠቃሚዎች እድሜን እንዲያሳውቁ ማድረግን ጨምሮ ጥረት የማድረግ፤

6/ የተወሰኑ ይዘቶችን ከማሰራጨቱ በፊት የተጠቃሚዎችን እድሜ የማሳወቅ፤ የይዘቶቹን ባህሪ የተረዱና አደጋውን የተቀበሉ ብቻ እንዲጠቀሙ ምርጫ የመስጠት እንዲሁም እድሜያቸው ከ16 አመት በታች መሆኑን ለገለፁ ሕፃናት ይዘቶቹ ተደራሽ እንዳይሆኑ የመከልከል፤

7/ የአልኮል፣ የትምባሆና የተከለከሉ አነቃቂ ንጥረ ነገሮች ተጠቃሚነትን የሚያበረታታ ይዘት ከማተምና ከማሰራጨት የመቆጠብ፤

8/ በተፈጥሮው ወሲብ ቀስቃሽ የሆነ፣ በገንዘብ የወሲብ ድርጊት እንዲፈጸም የሚያበረታታ፣ ሕፃናትን ለወሲባዊ ጥቃት የሚያዘጋጅ እና በኤሌክትሮኒክ ኮሚዩኒኬሽን አማካይነት የሚፈጸም ትንኮሳን የያዘ ይዘት ከማተምና ከማሰራጨት የመቆጠብ፤

9/ የተጠቃሚዎችን ዳታ የመጠበቅ፤ ለሦስተኛ ወገኖች አሳልፎ ለመስጠት የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲከሰቱም የተጠቃሚዎችን ግልፅ ፈቃድ አስቀድሞ የማግኘት፤

10/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑን በመጠቀም ለሚከናወን ግብይት የአገሪቱን የኤሌክትሮኒክ ግብይት ሕግ አክብሮ የመንቀሳቀስ፤

11/ ከተጠቃሚዎች ጋር በሚገባው ውል ተፈጻሚ የሚሆኑ ግዴታዎችን በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ ላይ በግልፅ በሚታይ መልኩ ማሰራጨትና ለተጠቃሚዎች እንደ ማስረጃ እንዲያገለግል ኤሌክትሮኒክ ቅጂ የመስጠት፤ ተፈጻሚ የሚሆኑ ግዴታዎች ላይ ለውጥ ሲኖር በ48 ሰዓት ውስጥ ለተጠቃሚዎች በማሳወቅ በድጋሜ ፈቃድ የመጠየቅ፤

12/ የተሳሳተ መረጃና የኮምፒዩተር ጥቃትን መፍጠር፣ ማተምና ማሰራጨትን ጨምሮ ኢንተርኔትን መሠረት ካደረጉ ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎች የመታቀብ፤ እና፣

13/ የጽሑፍ ይዘቶችን ከታተሙበት ጊዜ ጀምሮ ለ1 አመት ያህል እንዲሁም ለኦዲዮና ቪዲዮ ደግሞ ለ6 ወር በማኅደር የማቆየትና በቀላሉ ተፈልገው እንዲገኙ "የፈልገው ያግኙ" አገልግሎት የማካተት፡፡

## 15. *<u>በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን የሚገለፁ መረጃዎች</u>*

1/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ በድረ-ገጹ "ስለ እኛ" በሚለው ክፍል ወይም ስለ ድርጅቱ መሠረታዊ መረጃ በሚሰጥበት ተመሳሳይ ስያሜ ባለው ክፍል፡-

ሀ) የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑን ስም፣

ለ) የባለቤቱን ስም፣ አጭር ግለ ታሪክ፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር፣ የኢሜይል አድራሻ፣

ሐ) የዋና አዘጋጁን ስምና የሚገኝበትን ዝርዝር አድራሻ፣

መ) የተሠራጨበት ወይም ታተመበት ቀንና ሰዓት፣

ሠ) መረጃው የተሻሻለ ከሆነ የተሻሻለበት ቀን ወይም ጊዜ፤

መግለፅ አለበት፡፡

2/ ተጠቃሚውን አሳታፊ የሚያደርግ ይዘትን የሚያሠራጭ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ከሆነም ከላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ በድረ-ገፁ ላይ፡-

ሀ) የይዘቱ ጸሐፊ፣ አሳታሚውና ሌሎች በይዘቱ አመንጪነት የተሳተፉ ሰዎች፣

ለ) በኢትዮጵያዊያን አቆጣጠር ይዘቱ ድረ-ገጹ ላይ የተጫነበት ቀን፣ ወር፣ ዓመተ ምሕረት እና ሰዓት፣ እንዲሁም

ሐ) ይዘቱ የተሻሻለበት ቀን፣ ወር፣ ዓመተ ምሕረት እና ሰዓት፤

መገለፅ አለበት፡፡

3/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ በድረ-ገፃቸው ላይ መገለፅ የሚገባቸውን መረጃዎች በማይገልፁበት ጊዜ በአዋጁ መሠረት ባለሥልጣኑ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በ14 ቀናት ውስጥ ግዴታቸውን እንዲወጡና የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ እንዲያሳውቁት ሊያስገድድ ይችላል፡፡

## 16. ስለዋና አዘጋጅ

1/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ዋና አዘጋጅ ከሾመ፤ ዋና አዘጋጁ፡-

ሀ) የተሟላ የሕግ ችሎታ ሊኖረው ይገባል፤

ለ) በድረ-ገፁ የሚሠራጩትን ዘገባዎች ይዘት የመቆጣጠርና ማንኛውም ነገር ያለፈቃዱ እንዳይሠራጭ የማድረግ ሥልጣን አለው፤

ሐ) በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ በተሰራጨው ይዘት ላይ ሙሉ የሕግ ተጠያቂነት አለበት፡፡

2/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪው፡-

ሀ) ዋና አዘጋጅ ካለው የዋና አዘጋጁን ስምና ዝርዝር አድራሻ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

ለ) የዋና አዘጋጁን ስም፣ አድራሻ፣ የቢሮ ስልክ፣ የኢሜል አድራሻ እና ከበየነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ ጋር የሚገናኙ የማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን አድራሻ መገኛ፣ ማስፈንጠሪያ በድረ-ገጹ የአድራሻ መጠቆሚያ ወይም ስለ ድርጅቱ መሠረታዊ መረጃ በሚሰጥበት ክፍል ማካተት ይኖርበታል፡፡

## 17. ለውጦችን ስለማሳወቅ

የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪው በምዝገባ ወቅት ባቀረባቸው ማናቸውም መረጃዎች ላይ ለውጥ ሲያደርግ እንዲሁም አገልግሎቱን ሲያቋርጥ በ14 ቀናት ውስጥ ለውጡን ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 18. እርማት ወይም መልስ የመስጠት ግዴታ

1/ በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን በቀረበ ዘገባ መልካም ስሙና ክብሩ በሐሰት ወይም በአሉታዊ ጎኑ ተጎዳብኝ የሚል ማንኛውም ሰው ቅሬታ የፈጠረው ዘገባ ከተሰራጨበት ቀን ጀምሮ ባለው 3 ወር ጊዜ ውስጥ ዘገባው በቀረበበት የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን በተመጣጣኝና በተመሳሳይ ጊዜ በግልፅ ያለ ክፍያ እርማት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

2/ ቅሬታ የቀረበለት የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ የቅሬታ አቅራቢውን መብት ሊያከብር እና የሚያቀርበውን እርማትም፡-

ሀ) የጎትመት ውጤት ከሆነ በእርማቱ ወይም ምላሹ በደረሰ በ24 ሰዓት ውስጥ፣

ለ) ፕሮግራም ከሆነም በ5 ቀናት ውስጥ በተመጣጣኝና በተመሳሳይ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ገፅ ያለ ክፍያ ሊያስተላልፍለት ይገባል፡፡

ሐ) እርማቱን ለማስተላለፍ ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለገውም ለ3 ሳምንት ብቻ በማራዘም እርማቱን ማስተላለፍ ያለበት ሲሆን፣ የዘገየበትን ምክንያትም በስልክ ወይም በደብዳቤ ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ ይኖርበታል።

3/ እርማት የማውጣት ወይም መልስ የመስጠት መብቱን የተነፈገ ሰው አገልግሎት ሠጪው ተገዶ መልሱን እንዲያወጣለት ለፍርድ ቤት ወይም ለባለሥልጣኑ ወይም ለመገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

## 19. *ጥቆማ፣ ቅሬታና ግብረ መልስን ስለማስተናገድ*

የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪው፡-

1/ በሚያሠራጨው ኘሮግራም ወይም ፅሁፍ ስህተት ሲገኝ ለማረም የሚያስችለውን የአሰራር ሥነ-ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፣

2/ ከአድማጭ ወይም ተመልካቾች የሚቀርብ ቅሬታን ተቀብሎ ማስተናገድ ይኖርበታል፣

3/ ከባለሥልጣኑ ለሚቀርለት ግብረ መልስ ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ የወሰደውን ማስተካከያ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 20. *የአገልግሎት ክፍያዎችን ስለመክፈል*

የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው ተመን መሰረት የምዝገባ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡

## ክፍል አራት
## ስለአስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃዎች

### 21. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅን ከተላለፈ በመገናኛ ብዙሃን አዋጁ በተመለከተው መሠረት ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በየደረጃው ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ለ) እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት መጣል፤ እና

ሐ) የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማገድ ወይም መሰረዝ፡፡

### 22. አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣን

1/ የምዝገባ የምስክር ወረቀትን የማገድ እና የመሰረዝ አስተዳደራዊ እርምጃዎች የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ቦርድ ይሆናል፡፡

2/ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት እና የገንዘብ ቅጣት የመጣል አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

3/ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚወስድ አካል አስተዳደራዊ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት፡-

ሀ) ለአገልግሎት ሠጪው ጥፋል የተባለውን ጉዳይ፣ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊጣልበት እንደሆነ፣ ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን እና የጊዜ ገደብ በፅሁፍ ማሳወቅና አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፤

ለ) የአገልግሎት ሠጪውን አጠቃላይ የገንዘብ ሁኔታ፣ በጥፋቱ ምክንያት ያገኘውን የገንዘብ ጥቅም፣ ሕግና መመሪያዎችን የማክበር እና ግድፈቶችን የመፈጸም የኋላ ታሪክ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት፤ የገንዘብ ቅጣቱ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

### 23. የይግባኝ አቀራረብ

1/ ባለሥልጣኑ በወሰነው አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ ውሳኔው በደረሰው በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ቦርዱ አቤቱታው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

2/ ቦርዱ በወሰነው አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ ውሳኔው በደረሰው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡

3/ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርዱ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## 24. *በፍርድ ቤት የሚወሰዱ እርምጃዎች*

1/ የስም ማጥፋት ተግባር በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ሲፈፀም በፍትሐብሔር ኃላፊነት እስከ 300,000 ብር (ሦስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የህሊና ጉዳት ካሳ ሊያስቀጣ ይችላል፡፡

2/ የወንጀል ተግባር በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን በመፈፀሙ የወንጀል ክስ ሲቀርብ፡-

ሀ) የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪው የምዝገባ የምስክር ወረቀት በፍርድ ቤት ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ፤ ወይም፣

ለ) ጥሰት የተፈፀመበት ፕሮግራም ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

## 25. ስለ ይርጋ

በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አማካይነት ለሚፈፀም ጥፋት ጥፋቱ የተፈፀመበት ይዘት በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ ከተሠራጨበት ቀን ጀምሮ ባለው 3 ወር ጊዜ ውስጥ ምርመራ ካልተጀመረ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

# *ክፍል አምስት*
# *ልዩ ልዩ ድንጋጌ*

## 26. *የፈቃድና ምዝገባ ሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት*

1/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን የምዝገባ ሥራዎች የሚከናወኑት በባለሥልጣኑ ውስጥ በተቋቋመ መደበኛ የመገናኛ ብዙሃን የፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ነው፡፡

2/ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍሉ፡-

ሀ) አመልካቾችን ይመዘግባል፤ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

ለ) መገናኛ ብዙሃን ለአገልግሎት ተጠቃሚዎች በቀላሉና በቀጥታ ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪውን ስም፣ አድራሻ፤ የስልክ ቁጥር፣ የኢሜልና የድረ-ገፅ አድራሻ፣ የመገናኛ ብዙሃኑን ዋና አዘጋጅ ስምና ስልክ ቁጥር በመመዝገብና በማጠናቀር በባለሥልጣኑ ድረ-ገፅ ተደራሽ ያደርጋል፤

ሐ) የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ለሚጠይቋቸው የድጋፍ ጥያቄዎች ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

መ) ሌሎች ተያያዥ ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## 27. የባለሥልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት

1/ በአዋጁ አንቀፅ 6(3)፣(4)፣(5)፣(11)፣ አንቀፅ አንቀፅ 27 እና ሌሎች የአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃንን በመመዝገብና የምዝገባ ምስክር ወረቀት በመስጠት ሕጋዊ እውቅና ይሰጣል፤

ለ) የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን የምዝገባ አገልግሎት ክፍያን መንግሥት በሚያጸድቀው ተመን መሠረት ይሰበስባል፤

ሐ) የበይነ መረብ መገናኛ ብዙሃን ሥራቸውን በሕግ አግባብ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ በሕገ መንግሥቱ፣ በመገናኛ ብዙሃን አዋጁና በአዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንብ፣ መመሪያ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

መ) የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃኑ በድረ-ገፃቸው ላይ መግለፅ የሚገባቸውን መረጃዎች በማይገልፁበት ጊዜ ባለሥልጣኑ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በ14 ቀናት ውስጥ ግዴታቸውን እንዲወጡና የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ እንዲያሳውቁ ይጠይቃል፤

ሠ) በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤

ሰ) ከኅብረተሰቡ የሚቀርቡ ቅሬታና ጥቆማዎችን በመመርመር አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል፤

ሸ) የተሠራጨ ይዘትን በመከታተልና በመገምገም ሕግን የተላለፈ ሥርጭት ሲኖር እንዲያስወግድ በጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡

2/ ኅብረተሰቡ በባለሥልጣኑ ድረ-ገፅ ወይም አጭር የስልክ መስመር አማካኝነት ጥቆማና አቤቱታ የሚያቀርብበት ምቹ፣ ቀላልና ተደራሽ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

3/ ፕሮግራሙን ያሠራጨው ሰው በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት እርምጃ ካልወሰደ አግባብ ካለው የመንግሥት አካል ጋር በመተባበር ሕገ ወጥ ስርጭቱ እንዲቆም ያደርጋል፡፡

4/ የተሰራጨው ይዘት የወንጀል ጥፋትን የሚያስከትል ከሆነ ድርጊቱን በፈፀመው ሰው ላይ የወንጀል ክስ እንዲመሰረት ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፡፡

5/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን የሥነ-ምግባር መመሪያ በማውጣት ያስፈፅማል፡፡

6/ በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን የሚሠራጩ መረጃዎችን ይዘት ታማኝነትና እውነተኛነትን ለማረጋገጥ ተጠቃሚውን ሕዝብ ስለአጠቃቀሙ ሥነ-ምግባርና ልዩ ልዩ መመዘኛዎች ወይም ስታንዳርዶች በማስተማር የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ያሳድጋል፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ንቅናቄ ይፈጥራል፤ የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም ባህል ወይም ሚዲያ ሊትረሲን ያጎለብታል፤

28. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

የመገናኛ ብዙሃን አዋጅና ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ሰዎች በዚህ መመሪያ መሠረት በባለሥልጣኑ በመመዝገብ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማግኘትና በሚመለከተው የንግድ ቢሮ የንግድ ፈቃድ ማውጣት ይኖርባቸዋል፡፡

29. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

1/ የባለሥልጣኑ ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ በረቂቅ መመሪያው ዝግጅት የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ያረጋግጣል፤ በቦርዱ የፀደቁ መመሪያዎችንም አሳትሞ ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

30. <u>መመሪያው የፀና ስለመሆኑ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ሥራ አመራር ቦርድ ከጸደቀበት ከግንቦት 9 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ሥራ አመራር ቦርድ*